ኅዳር 2 ቀን 2013 ዓም

# «ሰነፍ እረኛ ከቅርብ ትቶ ከሩቅ ይመልሳል»

በወያኔ ከፍተኛ አመራሮችና የስለላው መዋቅር አባላት ላይ የጠነከረ ሕጋዊ እርምጃ መወሰድ የነበረበት፤ ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓም ለለውጡ አመራሮች የአዲስ አበባ ሕዝብ ድጋፍ ለማሳዬት በከፍተኛ ብዛት በወጣበት ወቅት፣ ዶር ዐቢይን ለመግደል ሙከራ በተደረገ ቅጽፈት ነበር። ያንም ለማድረግ አብሮ የበላና የጠጣ፣ ለዚህ ማዕረግ ባበቁት ሰዎች ላይ ኀሊናው አልቆርጥለት አለ እንበል። የትግሬ-ወያኔ ቅጥረኛ የሆኑ የቅማንት ማንነት ኮሚቴ አባሎችን አስታጥቀው ከዘጠና ሺ በላይ ዐማራ ለሞትና ለመፈናቀል ሲዳረግ፤ በአጥፊው ቡድን ላይ እርምጃ መውሰድ አልተፈለገም። አሽከራቸውን የሶማሊያውን ፕሬዚደንት መሣሪያ አድርገው ከፍተኛ የሆነ የሕዝብና የንብረት ዕልቂት ሲፈጽሙም በአጥፊ ቡድኑ ላይ እርምጃ ለመውሰድ አልታሰበም። በጋምቤላ፣ በቤንሻጉል ጉምዝ ክልል በተደጋጋሚ በዐማራ ሕዝብ ላይ ጅምላ ጭፍጨፋ ሲደረግም አሁንስ በዛ አልተባለም። የትግሬ-ወያኔ ዘረኛ ቡድን ከኦነግ ሼኔ ጋር እጅና ጓንት ሆኖ፤ በኦሮሚያ በሚባለው አካባቢ በዐማራና በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ላይ ዘግናኝ የዘር ፍጅት ሲፈጸም አሁንም መንግሥት የመንግሥትነት ኀላፊነቱን አልተወጣም። ይባስ ተብሎም የዘር ፍጅቱን በስሙ ለመጥራት አልተፈለገም። ይህ አሳዛኙ የዐማራ ሕዝብ የእግር ውስጥ እሳት ሆኖ የሚዘልቅ ነው።

የትግሬ-ወያኔ ቡድን ከማዕከላዊ መንግሥቱ አፍንግጦ፣ ማዕከላዊ መንግሥቱን የሚገዳደር «የፌዴራሊስት ኀይሎች ነን» ያሉትን በተደጋጋሚ መቀሌ እየሰበሰበ፣ እያስታጠቀና እያደራጀ ማነው የሚደፍረኝ? ሲል ከመንግሥት ወገን የተሰማ ሕግንና ሥርዓት የማስከበር ሥራ በተግባር አልታየም። አልተሰማም። «ሕገ-መንግሥቱ»ን ምንጊዜም የትግሬ-ወያኔ አሸባሪው ቡድን አክብሮት እንደማያውቅ አያሌ ማሳያዎች ቢኖሩም፣ ባደባባይ በነባር አሠራራቸው ቁጭ ብለው እጃቸውን አውጥተው የመረጡትን ዶር ዐቢይን «አሀዳዊና አምባገነን ቡድን፣ ነፍጠኛ እና ዳግማዊ ኀበና» በማለት ፈርጀው በትጥቅ፣ በሤራና በገንዘብ የታገዘ የተቀነባበረ ዘመቻ ሲፍቱ፣ አቁም ያለና የመንግሥት ብቸኛ መጠቀሚያ የሆነውን «ኀይል የመጠቀም መብቱን» ሲጠቀም አላየንም። የፌዴሬሽን ምክር ቤት እና የምርጫ ቦርድ ወሳኔዎችን አንቀበልም ብለው፤ ምርጫ አካሂደው «መንግሥት ነን» ሲሉ፤ የአገሪቱ ፓርላማም ሆነ መሪዎቹ ያሉት አንዳች ሕግና ሕጋዊነትን የሚያስከብር እንቅስቃሴ አላደረጉም። ሌላው ቀርቶ ወያኔ ትውልዱን አስታጥቆና አሰልጥሎ ለመዋጋት ዝግጁ መሆኑን የሚያሳይ የኀይል ማሳያ ሠልፍ ሲያደርግ፤ ለምን? ያለ የለም። እነዚህ ሁሉ ሁነቶች የአገርን አንድነት፣ የሕዝብን ሉዐላዊነት የሚጻረሩ ድርጊቶች ናቸው። እነዚህ ደግሞ የአንድ አገር ማዕከላዊ ብሔራዊ ጥቅም መገለጫዎች ናቸው። በነዚህ ላይ ድርድር የሚባል ነገር የለም። በኀይል የመጣን በኀይል ገፍትሮ መመለስ እና ማንበርከክ በዓለም አቀፍ ሕግ ተቀባይነት ያለው ነው። የመንግሥት ዓይነተኛ ሚናም ይህን በአግባቡ መወጣት ነበር።

ዛሬ በዐቢይ አሕመድ የሚመራው መንግሥት በትግሬ-ወያኔ አባላት ላይ እየወሰደ ያለው እርምጃ ሕግና ሥርዐትን ለማስከበር የሚል መርሕ የሚከተል እንደሆነ ቀደም ሲል፤ በመከላከያ ሚኒስትሩ በኋላም በጠቅላይ ሚኒስትሩ እየተነገርን ነው። የመከላከያ ሚኒስትሩ የዐማራ ልዩ ኀይልና ሚሊሻ ከሠራዊቱ ጎን ሆኖ ከፍተኛ መስዋዕትነት በመክፈል፣ ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ሠቲት ሑመራና ማይካድር ላይ የሠፈረውን የትግሬ-ወያኔ ዘረኛ ቡድን ድባቅ መትተው፣ ከተከዜ ወዲህ ያሉትን የዐማራ እርስቶች ነፃ ባወጣበት ሰዓት በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብለው፤ በትግራይ ክልል ሠራዊቱ የሚያደርገው ተጋድሎ «ሕግና ሥርዓት ማስከበር እንጂ፤ ወሰንን ለማስመለስ አይደለም» ሲሉ ተደምጠዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከማይክርዳ ጉብኝ በኋላ «ጁንታውን የመደምሰስ እንጂ፣ ርስት (ግዛት) የማስመለስ አይደለም።» ሲሉ በፊት-መጽሐፋቸው አስነብበውናል። ሕግና ሥርዐት ማስከበርማ ድሮ ቀረ። ሕገ-መንግሥቱን ከማንም ቀድሞ የሻረው የትግሬ-ወያኔ ቡድን ነው። ወደው በመረጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ላይ የግድያ ሙከራ ባደረጉ ዕለት የውንብድና ሥራ ሠርተዋል። የዚያን ጊዜ ነበር ሕግና ሥርዐት ማስከበር። ዕንቁላል እየሠረቀ ሲያመጣላት የት አገኘኸው ብላ ሳትጠይቅ እየቀቀለች በልታ፣ ልጁ ከዕንቁላል ወደ በሬ ሥርቆት ተሸጋግሮ ሲያዝ አዎይ ልጄ ብላ ስታለቅስ፤ የተገረመው ልጅ፤ «አዬ እናቴ አሁን ለቅሶሽ ምን ይጠቅማል? በዕንቁላሉ በቀጣሽ ኖሮ ከዚህ አልደርስም ነበር»፤ እንዳላት አበው ያስተምሩናል። በአሁኑ ጊዜ በዶር ዐቢይ የሚመራው መንግሥትና ሕዝብ እየወሰደ ያለው እርምጃ እጅግ የዘገየና የብዙ ሰዎችን ሕይወት ከቀጠፈ፣ ንብረት ከወደመ፣ ቤቶች እና ቤተ እምነቶች በእሳት ከጋዩ በኋላ እየተወሰደ ያለ በመሆኑ «በቅርብ መመለስ የሚቻለውን ብዙ እርቀት ተጉዞ ለመመለስ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው። ይህ እንቅስቃሴም የአያሌ ጀግኖችን ሕይወት የጠየቀ ሆኗል። የሠራዊቱና የሕዝቡ በዚህ ወቅትና ሰዓት በትግሬ-ወያኔ ላይ የተጀመረው ዘመቻ፣ ሕግና ሥርዓትን ለመታደግ ሳይሆን፤ ሥልጣንን ለመታደግ እንደሆነ ሒደቱ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ሕግና ሥራዓት የማስከበሩማ ቀደም፤ ጧት ቀረ።፣ ሥርዓትና ሕግና ከተጣሱ ውለው አደሩ።

በትግሬ-ወያኔ ላይ መወሰድ የነበረበት ሕጋዊ እርማጃ መዘግየት ማለት «በቅርብ ትቶ በሩቅ መመለስ ነው»። ይህ ደግሞ ዋጋ እያስከፈለ ነው። በማይካድራ በንፁኀን ዜጎች ላይ የተፈጸመው የዘር ፍጅት፣ በሰሜን ዕዝ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ላይ የተፈጸመው ግፍ የተሞላበት ዘግናኝ ጭፍጨፋ፣ የደረሰው የንብረትና የጦር መሣሪያ ውድመት፣ ባሕርዳር እና ጐንደር ላይ የደረሰሰው የሮኬት ጥቃት፤ ዘረኛውን የፋሽስት ቡድን የትግራይን ሕዝብ ምሽግ ሳያደርግ በጧት የሚመጥነውን ቦታ እንዲይዝ ባለመደረጉ የተፈጠረ ችግር እንደሆነ መጠራጠር አይቻልም። ይህን ዘረኛ ቡድን ዘግይቶም ቢሆን፣ ለፍርድ ለማቅረብ በዐማራ ልዩ ኀይልና ሚሊሻ እንዲሁም በመከላከያ ሠራዊቱ እየተወሰደ ያለው እርምጃ የሕይዎት፣ የአካልና የገንዘብ ኪሣራን ማስከተሉ እርግጥ ነው። ይህም ከቅርብ ትቶ ከሩቅ የመመለስ ስልት፣ ጠላት በዋለ ባደረ ቁጥር ምን ሊያስከትል እንደሚችል ከርቀት የመመልከት ችግር እንደሆነ ሁኔታዎች አሳይተዋል።

እንዳው ከመቅረትና የትግሬ-ወያኔ ቡድን ራሱን አደራጅቶ እንደገና ወደ ሥልጣን ማማው ለመዝለቅ እያደረገ ያለውን፣ ግን እስካሁን ያደረሰውን ጥፋት ሳያጠፋ መቆጣጠር የሚቻልበት ወርቃማ ጊዜ ቢያልፍና ከፍተኛ መስዋዕትነት ቢያስከፍለንም፤ ይህን አረመኔ ቡድን የመጨረሻ እስትንፋሱን ማቋረጥ ተገቢ ነውና፣ እንቅስቃሴው መደገፍ ያለበት ነው። ሕዝቡ ለሠራዊቱ፣ ለልዩ ኀይሉ እና ለሚሊሻው አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ በማድረግ የዜግነት ግዴታውን ሊወጣ ይገባል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ግን መወሰድ ያለባቸው ወሳኝ ጉዳዮች አሉ። እነዚህም፦

1. በዐማራ ልዩ ኀይል፣ ሚሊሻና በመከላከያው ሠራዊቱ ጥምረት እና ውድ የሕይወት ዋጋ ተከፍሎ ከትግሬ-ወያኔ አገዛዝ ነፃ የሆኑት ወልቃይት፤ ጠገዴ፣ ጠለምት፤ ሠቲት-ሑመራ እና ራያ አዘቦ ወደ ጥንት ማንነታቸውና ክፍለ-ሀገሮች መመለስ አለባቸው።
2. ከላይ ከተጠቀሱት አማራጮች ውጪ አካባቢዎቹ፣ በጊዜአዊነት ለተሰየመው በዶር ሙሉ፣ ዶር አረጋዊ በርሀ፣ አብርሃ ደስታና ስዑል ለሚመራው የትግራይ ብልጽግና ቡድን የሚተላለፉ ከሆነ ዐማራው ለሦስተኛ ጊዜ የተከዳ መሆኑ ማሳያ ነው።

ስለሆነም ሕዝቡ የሚፈልገውና የታገለበት፣ ልጆቹን የሰዋበት፣ የተሰደደበትና ሥቃይ ያየበት ትግል ፍሬ-አልባ እንዳይሆን፣ በጥቅሉ ዐማራው፣ በተናጠል በዐማራ ስም የተደራጁ ድርጅቶች ከሕዝባችን ፍላጎት ውጭ ምንም ነገር እንዳይሠራ ነቅተው መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ለዚህም ሙሉ ኀላፊነቱን የዐማራው አዴፓ/ብልጽግና አቶ አገኘሁ ተሻገርና ቡድኑ፣ እውነተኛ ዐማራዎች መሆናቸው መፈተኛቸው አውራ ጉዳይ ይህ መሆኑን ዐውቀው፣ ከሕዝቡ ጎን እንዲቆሙ መወትወትና ማሳሰብ የግድ ነው።

ከዚሁ ጋር የትግሬ-ወያኔ ጎንደርን፣ ጎጃምን፣ ወሎንና ሸዋን በተቆጣጠረ ጊዜ፦

- የከተሞችን ጄኔሬተሮች፣ ምሳሌ የጎንደር ከተማን፣ የጎርጎራ ከተማን፣ የጣና በለስን ወዘተ ነቅሎ ወስዷል።
- የትምህርት ቤቶችን ወንበርና ጠረጴዛዎች፣ ኮምፒዩተሮች፤ ታይፒ ራይተሮች፣ ጠቅሎ ወስዷል፤
- የከተሞችን የመብራት እና የውኃ ቆጣሪዎችን ነቃቅሎ ወስዷል።
- የመንግሥታዊና የሕዝባዊ ድርጅቶችን የመድኃኒት ክምችቶችን በሙሉ ዘርፎ ወስዷል፤
- በየክፍለ-ሀገሮቹ የነበሩ ባንኮችን ገንዘብ ዘርፏል፤
- የወጣቶች፣ ሴቶች፤ ገበሬዎችና የከተማ ነዋሪዎች ንብረቶችንና ገንዘብ በሙሉ ዘርፏል፣
- የመንግሥትና የሕዝብ ተሽከርካሪዎችን ዘርፎ ወስዷል፤
- የጎጃምን የአውራ ጐዳና የጠጠር መፍጫ ማሽነሪ ነቅሎ ትግራይ ወስዷል፤
- በጥቅሉ በአራቱ ክፍለ-ሀገሮች ይገኙ የነበሩ ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ የሕዝብ፣ የመንግሥትና የማኅበራት ንብረቶች እንደጠላት እና ምርኮኛ ንብረት ቆጥሮ ወደ ትግራይ አጕዟል። በዚህ የወያኔን ቊንጮ ባለሥጣኖችና ተባባሪዎቻቸውን በሕግ ቊጥጥር ሥር ለማዋል ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን በዘረፋ የተወሰዱት ንብረቶች እንዲመለሱ መደረግ አለበት እንላለን። ዛሬ የኤፈርት ንብረት የሆኑት፣ ድርጅቶች፣ ፋብሪካዎች እና የተገነቡ ተቋሞች ምንጫቸው ከሕዝብና ከመንግሥት የተዘረፈ ንብረት መሆኑ ታውቆ፣ ሌላው ቢቀር፣ የትግሬ-ወያኔ ባለሥልጣኖች ቤትና ንብረቶች፣ የኤፈርት ድርጅቶች በሙሉ የሕዝብና የመንግሥት እንዲሆኑ ሥራዎች መጀመር አለባቸው።

ድል ለሠፊው ሕዝብ!

ዐማራው ህልውናውን በትግሉ ያረጋግጣል!